

ግርማቸው ለማ



# ኢትዮጵያ

ነሐሴ 2004 | 1ኛ ዓመት ቁጥር 2 | በነጻ የሚሰራጭ


## ኢሀአፓ 40ኛውን የምስረታ በአል መስከረም 1 ያከብራል

## «41ኛውን የምስረታ በአል በአገራችን ለማክበር እንጣር»

### አቶ እያሱ አለማየሁ



ኢሀአፓ 40ኛ አመት የምስረታ በዓሉን በመጪው ሴፕቴምበር 1/2012 እዚህ ዋሽንግተን ዲስ ውስጥ በደማቅ ሁኔታ ለማክበር በዝግጅት ላይ ይገኛል::

በዓሉ፣ 16ኛው መንገድ ላይ በሚገኘው ሴንት ጆርጅ አዳራሽ ፣ ቅዳሜ ዕለት ከ5 ሰአት ጀምሮ የሚከበር ሲሆን፣ በዚህ ታሪካዊ በአል ላይ፣ በዋሽንግተን እና አካባቢው የሚገኙ የኢሀአፓ አባላት እና ደጋፊዎች፣ ከተለያዩ ዓለማት የሚመጡ አባላት እንዲሁም ተጋባዥ እንግዶች የሚገኙ መሆናቸውን ለመረዳት ተችሏል::

በድርጅቱ 40ኛ ዓመት የልደት በዓል አከባበር ላይ አንጋፋ የድርጅቱ አባላት ይገኛሉ ተብሎ ይታመናል ።ዕለቱን በደመቀ ሁኔታ ለማክበር ኃላፊነቱን የወሰደው ዲሲ የሚገኘው የኢሀአፓ ኮሚቴ፣ ከፍተኛ ዝግጅት ያደረገ ሲሆን፣ በዕለቱ የሚቀርቡ ትዕይንቶችም ለዝግጅቱ ታላቅ ድምቀት እንደሚሰጡት የኮሚቴዉ አባላት ያላቸዉን እምነት ከወዲሁ ገልጸዋል::

ኢሀአፓ የተመሰረተው በኢትዮጵያዉያን የዘመን አቆጣጠር በ1964 ዓ.ም ሲሆን፣ ራሱን ይፋ ያደረገው ደግሞ በ1967ዓ.ም ነው:: በወቅቱ፣ መሬት ላራሹና ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት በሚሉ ዐቢያን መፈክሮች ሥር እእላፍ የአገሪቱን ወጣቶች አሰልፎ ለለውጥ የታገለዉ ይህ ታላቅ ድርጅት ስልጣን ላይ የነበረዉ ወታደራዊ መንግስትና ወያኔ ተረባርበዉ በከፈቱበት ጥቃት ከፍተኛ ጉዳት የደረሰበት መሆኑ ይታወቃል:: ይሁንና ያን ሁሉ ዉርጅብኝ አልፎና ድርጅታዊ ህልዉናዉን ጠብቆ 40ኛ ዓመቱን ለማክበር መብቃቱ ድርጅቱ ያለውን ታላቅ ጥንካሬ የሚያመለክት መሆኑን የታሪክ ታዛቢዎች ይስማሙበታል::

ኢትዮጵያ ጋዜጣ በዚህ እትሟ፣ የድርጅቱን 40ኛ ዓመት በተመለከተ ከአንጋፋው ገጣሚና ደራሲ እንዲሁም ከድርጅቱ ከፍተኛ አመራር ከሆነው ከአቶ እያሱ አለማየሁ ጋር ያደረገችውን መጠይቅ ይዛ ቀርባለች:: አቶ እያሱ እንደተለመደው ጋዜጣዋ ላቀረበችለት ጥያቄ አጠር ያለና ግልጽ ምላሽ የሰጠ ሲሆን፣ 40ኛውን ዓመት በተመለከተ ለኢትዮጵያውያን የሚያስተላልፉት መልእክት እንዳለ ተብሎ ለተጠየቀው ጥያቄ፣ «41ኛውን በአገራችን ለማክበር እንጣር» ሲል ምላሽ ሰጥቷል::

**<<መፍትሔው ምንድን ነው?>>**

ሙስሊሙ ማህበረሰብ በዋሽንግተን የተቃውሞ ሰልፍ አደረገ::

ገጽ 4

**ዝግጅቱ በእጅጉ የተሳካ ነበር፤**

ኢወክንድ የድጋፍ ማሰባሰቢያ ታላቅ የእራት ምሽት አደረገ::

ገጽ 4

የዋንጫው አሸናፊ የሜሪላንድ ቡድን የምሳ ግብዣ ተደረገለት

ገጽ 8

**ቶምቦላው ወጣ!**

አውስትራሊያ የአንደኛው ዕጣ አሸናፊ ሆነ::

ገጽ 3







# ኢትዮጵያ

በኢሕአፓ የዲሲ ሪጅን ደጋፊ ኮሚቴ

የሚዘጋጅ ወርሃዊ ጋዜጣ



አድራሻ 5309 Georgia Ave. NW. 2nd fl. Washington DC 20011

ስ/ቁ 202 291 4217 ኢሜይል dc.region.eprp@gmail.com


## <u>ርዕሰ አንቀጽ</u>

# እንደወትሮዉ ሁሉ፤ዛሬም ኢትዮጵያዊነት አቸንፏል

በዕድሜ በከበረዉ ታሪካችን ዉስጥ ኢትዮጵያዊነት ያልተፈተነበትና ያላለፈዉ የፈተና ዘመን ኩቶ የለም።በታዋቂዎቹ የጦር ጎራዎችም ሆነ በማይታወቁቱ አዉደ ዉጊያዎች የተካሄዱት ፍልሚያዎች ሁሉ ኢትዮጵያዊነትን ለመታደግ የተደረጉ ነበሩ ።የተቀረዉ ዓለም ከተስፋፊዎችና ከቅኝ ገዢዎች ጫማ ሥር ወድቆ ይማቅቅ በነበረበት ጊዜ ሳይቀር በነጻነት አንገታችንን አቅንተን ከትዉልድ ወደ ትዉልድ ለመሻገዝ ያበቃን ተዐምር ቢኖር ከምንም በላይ ሀገርንና ከሀገር ጋር የሚዛመዱትን ዕሴቶች አግዝፎ የማየቱ ሕዝባዊ እሳቤ ነዉ ። የሀገር ነጻነት አደጋ ላይ በወደቀባቸዉ ኢጋጣሚዎች ሁሉ ኢትዮጵያዊነት የክረምትን ጭጋግ ሰንጥቆ ብቅ እንደሚል የደመና ግላጭ ጮራ ማገጃ የሌለዉ ኃይል መሆኑ ደጋግሞ ታይቷል። ኢትዮጵያዊነት ጉልበትና ወረት የማይለምጡት ጽናት ነዉ። ባለፈው ወር በደቡባዊቷ የአሜሪካ ክፍለ ግዛት ፤ ዳላስ ከተማ ዉስጥ ኢትዮጵያዉያን በአንድነት በመቆም ያስመዘገቡት ደማቅ ድልም ከዚሁ ይዳመራል።

የኢትዮጵያዉያን ህብረትና አንድነት በታየበት ሥፍራ ሁሉ በታኝ የሤራ ወጥመድ አጥምዶ ከዜጎች መሃከል መቀየጥ ጸረ ኢትዮጵያዊው ወያኔ ተለይቶ የሚታወቅበት ባህሪ ነዉ ። በዚሁ በሀገር ቤት የነበሩትን አንጋፋ የሙያና ሕዝባዊ ማሕበራትን ባሽመደመደበት መሰሪ ስልት፤ የዕድሜ ባለጸጋዉን የሰሜን አሜሪካ የኢትዮጵያዉያን የባህልና ስፖርት ተቋም ለማፈራረስ ሞክሯል። ለዚህም ዓላማዉ ተፈጻሚነት በሼኩ አይዞህ ባይነትና የገንዘብ ድጋፍ በተበረታቱ ጥቂት ደካማ ግለሰቦች አማካይነት ተለጣፊ የስፖርት ድርጅት በመፍጠር ውር ውር ሲል ታይቷል። ተመልካች አልገዛም እንጂ ፤ ተጫዋቾችን ተወዛዋገሮችንና ዘፋኞችን ለመከራዩት በሚልዮኖች የተቆጠረ የቱጃሩ ሼክ ዶላር ተረጭቷል።

በቱጃሩና በወያኔ መሃከል ያለዉ ትስስር ደግሞ አገር ያወቀዉ ጸሀይ የሞቀዉ ጉዳይ ነዉ። የዚያኑ ያህልም ቁርኝታቸዉ ከሸርክናም የምርጫ ካናቴራ ለብሶ ከመንነማለልም የሚያልፍ መሆኑ ይታወቃል። የወያኔ የጥቅም ድንበር የት ላይ እንደሚያበቃና የሼኩ የንግድ አዉታር ከዬት እንደሚጀምር በርግጠኛነት ለይቶ መናገር አይቻልም። ወያኔ ያቀደዉን ማስፈጸሚያዉ ከቱጃሩ ካዝና የሚወጣዉ (ዞሮ ዞሮ ከኢትዮጵያ ሕዝብ የሚገፈፈዉ ሀብት ) ነዉ። ወያኔ ለዕኩይ ተግባሩ በጥድፊያ ሲሰማራ የሼኩ ቦርሳ ዶላር አጭቆ ይከተለዋል ።

ይህን መሰሪ ቅንጅት በዉል የሚያዉቀዉ ኢትዮጵያዊ ከመላዉ የአሜሪካ ግዛቶችና ከሌላዉም የዓለም ክፍል ወደ ቴክሳስ በመትመም ላለፉት ሃያ ዘጠኝ ዓመታት የመሰባሰቢያ መድረክ ሆኖ ያገለገለዉን ፌዴሬሽን ቀጣይነት አረጋግጧል። ዉድድሮቹ የተካሄዱበት ስታዲየም **ከዚህ ቀደም ታይቶ በማይታዉቅ ሁኔታ ከአፍ እስከ ገደፉ በሕዝብ ብዛት ተጨናንቆ፤ ከክብር ሥፍራዋ ወርዳ በማታዉቀዉ ሰንደቅ ዓላማችን ዉብ ህብረ ቀለማት ደምቆ ሰንብቷል። በአንጻሩ ፤ የዋሽንግተን ዲሲዉ ዶላር በሽበሽ ዝግጅት ፤ ወና ከርሞ- መና ቀርቷል ። ቀደም እንደነበር ሁሉ ዛሬም ኢትዮጵያዊነት አቸንፏል።** ስንት ለስንት ብሎ ለሚጠይቅ ፤ የሚሰጠዉ መልስ " ሚልዮኖች ለባዶ/" ቢሆን ከእዉነት አያርቅም።

# *ደብዳቤዎች*

ለኢትዮጵያ ጋዜጣ አዘጋጆች የመጀመሪያ እትማችሁን ሳገኝ፣ እደጉ ተመንደጉ ብያለሁ በዚህች ጋዜጣ ለመሳተፍ ስለፈለግሁ፣ የምታትሙልኝ ከሆናችሁ፣ ድርሰቴ ደርሷችሁ በእትማችሁ እንድታወጡልኝልኪያታለሁ፡፡

ከመኮንን ውቤ

የየሩሳሌም እንግዳ

አቶ መኮንን የመጀመሪያ እትም ጋዜጣችንን አግኝተው በማንበብዎ እኛም ደስታችን የላቀ ነው፤ ይሁንና ልኬላችኋለሁ ያሏት ድርሰትዎ ግን አልደረሰችንም፤ ድርሰትዎን ባመችዎ ጊዜ ቢልኩልን ለማስተናገድ ዝግጁዎች መሆናችንን እናረጋግጥልዎታለን ።

## <u>በርቱ</u>

የመጀመሪያ እትም ጋዜጣችሁን አግኝቼ አንብቤያታለሁ፡፡ በርግጥም ጋዜጣችሁን እንዲህ ነው ብሎ ለመተቸትም ለማመስገንም ጊዜው አሁን አለመሆኑን አውቃለሁ፡፡ ቢሆንም ወደፊት ይህቹ የጀመራችኋት ጋዜጣ በይዘትም ሆነ በቅርጽ የአንባቢውን የመረጃ ጥማት የምታረካ እንድትሆን ምኞቴን እገልጽላችኋለሁ፡፡ በተረፈ እዚህ አሜሪካ ውስጥ መረጃንበማስተላለፉ በኩል ጋዜጣ ከሁሉም የበለጥ የተሻለ ነው እላለሁ፡፡ ምክንያቱም ሰው በረፍት ጊዜው ወይም በፈለገው አጋጣሚ መረጃውን ረጋ ብሎ ማንበብ የሚችልበት አጋጣሚ ይፈጠርለታልና፡፡ በተረፈ የተሻለ ስራ ለመስራት ያብቃችሁ በርቱ እላለሁ፡፡

እገሌ ከዋሽንግተን

## <u>ሁሌም ከጎናችሁ ነን</u>

የጋዜጣችሁ ስያሜ «ኢትዮጵያ» መሆኑን ስመለከት እንዲሁም የኢትዮጵያን ባንዲራ በጋዜጣዋ የፊት ገጽ ግራና ቀኝ ስመለከት እጅግ አድርጎ ደስ አለኝ፡፡ በዚህ ዘመን «ኢትዮጵያ» ለማለት የሚጠየፉ አያሌ ባንዳዎች በተፈለፈሉበት እና አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ባንዲራችንን ለማጥፋት ጭምር የሚጥሩ እንደ ወያኔ ያሉ ቅጥረኞች በነገሱበት፣ እናንተ የኢትዮጵያን ስምና ባንዲራ ከፍ በማድረጋችሁ ለኢትዮጵያ አገራችን ያላችሁን ቀናኢነት ያሳያል፡፡ እናም ሁሌም ከጎናችሁ መሆናችንን እናረጋግጥላችኋለን ጠንክራችሁ ሥሩ፡፡

ኢትዮጵያዊው ከዋሽንግተን

## <u>ሀይ የኢትዮጵያ ጋዜጣ አዘጋጆች</u>

እናንተ እንደእኔው አምባገነኖች እንደልባቸው በሚፈንጩበት አገር ተወልዳችሁ ያደጋችሁ ይመስለኛል፡፡ ሆኖም ግን ያፋኞችን ልጓም በመቃወም እዚህ ላለነው ኢትዮጵያውያን ይህን የመሰለ ጋዜጣ በማሳተም ለአንባቢያን ማቅረብ መቻላችሁ በጣም የሚያስመሰግናችሁ ነው፡፡ እደጉ ተመንደጉ እኛም ከጎናችሁ እንቆማለን፡፡

ነጻነት ከዲሲ


**አንድ መኝታ ቤት ቤዝመንት ውስጥ ለመከራየት ይፈልጋሉ?**

**እንግዲያው የራሱ መኝታ ቤት፣ መታጠቢያ እና ማዕድ ቤት ያለው እንዲሁም ከዋናው ቤት ጋር የማይገናኝ መውጫ እና መግቢያ ያለው ንጹህ ቤት 1138 Buchanan St. ላይ ያገኛሉ፡፡**

**ስልክ፡- (202) 726-1216**

## መፍትሔው ምንድን ነው?...

ይህ በእንዲህ እንዳለ፣ ወያኔ ሀበሽ የተሰኘውን ሀይማኖት በሙስሊሙ ወገን ላይ ለመጫን የሚያደርገውን የማስገደድ ተግባር በመቃወም ምዕመኑ መብቱን ለማስከበር የሚያደርገው እንቅስቃሴ ከጊዜ ወደጊዜ እያደገና አድማሱን እያሰፋ በመምጣት ወደተለያዩ የሀገሪቱ ክልሎች ጭምር እየተሰራጨ ከመምጣቱም በተጨማሪ፣ አሁን ሁኔታው ወደከፍተኛ ደረጃ ላይ እየተሸጋገረ መሆኑን ጉዳዩን በቅርብ የሚከታተሉ ታዛቢዎች እየገለጹ ይገኛሉ::

ወያኔ ደግሞ በበኩሉ፣ ሙስሊሙ ማህበረሰብ ሀይማኖቱን ከጥፋት ለማዳን የሚያደርገውን እንቅስቃሴ ለማፈን የተለያዩ እርምጃዎችን እየወሰደ ይገኛል:: በመሆኑም ሙስሊሙ ሃይማኖቱን ለማስጠበቅ የሚያደርገውን እንቅቃሴ ከአሸባሪነት ጋር ከማያያዙም በተጨማሪ፣ ኢያሌ ንጹሀን ዜጎችን አፍሶ እስር ቤት በመክተት እያሰቃየ፣ እየደበደበና ከፍተኛ ሰቆቃ እየፈጸመባቸው ይገኛል::

ወያኔ ከዚህም አልፎ ይህንኑ እያየለ የመጣበትን መብትን የማስከበር እንቅስቃሴ ከዚህ በፊት እንደሚያደርገው ሁሉ መሪዎችን ሰብስቦ በማሰር እንቅስቃሴውን አፍኖ ለማስቀረት፣ በሙሰሊሙ ዙሪያ የሚሰሩትን ጋዜጠኞች፣ አክቲቪስቶች፣ የሀይማኖት ምሁራንን፣ አርቲስቶችን ጨምሮ ስምንቱን የመፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴ አባላትን ሰብስቦ በማስር ድብደባ ከፈጸመባቸው በኋላ፣ በጸረ ሽብር ህግ ክስ መስርቶባቸዋል::

የታሰሩት የመፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴ አባላት፣ አቡበከር አህመድ የኮሚቴው ሊቀመንበር፣ ከሚል ሸምሱ የኮሚቴው ቃል አቀባይ፣ ያሲን ኑር የኮሚቴው አባል፣ ሼክ መከት ሙሄ የኮሚቴው አባል፣ አህመዲን ጀበል የኮሚቴው ቃል አቀባይ፣ አህመድ ሙስጠፋ የኮሚቴው ጸሀፊ፣ ሼክ ሱልጣን አማን የኮሚቴ አባል፣ ጀማል ያሲን የኮሚቴ አባል ናቸው::

ወያኔ እነዚህን የኮሚቴ አባላት ፣ ትላልቅ የሀይማኖት ሰዎችን፣ ጋዜጠኞችን፣ እና የመሳሰሉትን የሙስሊሙን የሙብት ትግል ይመራሉ ያላቸውን ሰዎች እስር ቤት በመክተት የሙስሊሙን ድምጽ ጸጥ ለማሰኘት ቢሞክርም፣ ሁኔታው ግን ወያኔ ከጠበቀው በተቃራኒ መሆኑ እየታየ ነው:: እንዲያውም ከዚህ የወያኔ ድርጊት በኋላ፣ አደባባይ የሚወጣው ህዝብ ቁጥር ከመቶ ሺዎች ወደ ሚሊዮኖች እየተሸጋገረ፣ የተቃውሞ አድማሱም ከአዲስ አበባ ወደተለያዩ ክልሎች በመዛመት ላይ ነዉ ። የህዝቡም የትግል ጽናት ከቀን ወደ ቀን እየጠነከረ በመምጣት ላይ ሲሆን፣ የታሰሩት የኮሚቴ አባላትም እኛ ብንታሰር ቀሪው ሙስሊም ሌላ እጥፍ ቁጥር ያለው ኮሚቴ መርጦ ትግሉን እንዲቀጥል ብለው ያስተላለፉት መልዕክት ለሙስሊሙ ይበልጥ ጽናት እንደሚሰጠው ብዙዎች ያምናሉ::

በመጨረሻም፣ ዋሽንግተን ዲሲ፣ ስቴት ዲፓርትመንት ፊት ለፊትየተቃውሞ ሰልፍ ያደረጉት የሙስሊም ማህበረሰብ አባላት ባስተላለፉት መልዕክት፣ በኢትዮጵያ ያለው ሁኔታ ከቀን ወደ ቀን እየከፋ በመምጣት ላይ መሆኑን፣ የወያኔ እመቃ የህዝቡን ቁጥር ማበራከቱን፣ የግለሰቦችና በጠቅላላው የህዝበ ሰባዊ ሙብት እየተጣሰ፣ የአምልኮና የመናገር ሙብቶች አደጋ ውስጥ መውደቃቸውን ጠቁመው፣ መላው አለም ይህንን በምስራቅ አፍሪካ እየደረሰ ያለውን ቀውስ ለማስቆምና ባካባቢው ሰላም ለማስፈን መንቀሳቀስ ብቻ ሳይሆን፣ የሀይማኖት ነጻነት እና ዴሞክራሲ እንዲሰፍን የማድረግ የሞራል ግዴታ እንዳለበትጠቅሰዉ፣ ሰላም ወዳድ የሆነው ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ከጎናቸው እንዲቆም በመጠየቅ ከዚህ የሚከተለውን ጥሪ አስተላልፈዋል፦

1ኛ.ወያኔ የሀገሪቱን ህገ መንግስት፤ የፈረማቸውን ዓለም አቀፍ የሰብአዊ ሙብት ህጎች እና የሙስሊሞችን ሙብት መጣሱን እንዲያቆም::

2ኛ.ባለፉት ጥቂት ወራት ወያኔ ያሰራቸውን፣ አክቲቪስቶች፣ መንፈሳዊ ሰዎችን፣ ጋዜጠኞችን፣ የኮሚቴ አባላትን እና ከህግ ውጭ ያሰራቸውን ተራ ዜጎች እንዲለቅ::

3ኛ.ወያኔ፣ ያገታቸውን እስረኞች በምን ሁኔታ ላይ እንዳሉ ቤተሰቦቻቸውና ዘመዶቻቸው እንዲያውቁ እንዲያደርግ እና እስረኞቹ ህክምና እንዲያገኙ እና በቤተሰቦቻቸው እንዲጎበኙ እንዲያደርግ::

4ኛ.የነጻ ፕረስን ሙብት እንዲያከበር እና ነጻ ጋዜጠኞች በህጉ መሰረት ሥራቸውን እንዲያከናውኑ:: ገጽ 8

## ቶምቦላው ወጣ!

ፍኖተ ህብረት የኢህአፓ ድምጽ እና ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ ሬዲዮ ለገንዘብ ድጋፍ ማሰባሰቢያ  ያዘጋጁት ቶምቦላ ዕጣ እሁድ ጁላይ 6/12 በድርጅቱ ጽ/ቤት አባላቱና ደጋፊዎቹ በተገኙበት  ወጥቷል::

በዚሁ መሰረት፣ አንደኛው ዕጣ አውስትራሊያ፣ ሁለተኛው ሲያትል፣ ሶስተኛው ሴንት ልዊስ፣  አራተኛው ደግሞ ሆላንድ ዉስጥ  ትኬቱን ለገዙ እድለኞች መው ጣቱን ከስፍራው በመገኘት ለማረጋገጥ ችለናል::

አሸናፊዎቹ  ዕጣዎች፣ አንደኛ ዕጣ አይፓድ፣ ሁለተኛ ኤች ዲ ቴሌቪዥን፣ 3ኛው ዕጣ ዲጂ ታል ካም ኮርደር፣ 4ኛው ዕጣ ደግሞ ልዩ ልዩ ሽልማቶች የሚያስገኙ ናቸዉ ።

ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ ሬዲዮ፣ በሳምንት ሁለት ጊዜ ረቡዕ እና እሁድ ከምሽቱ 2 ሰዓት እስከ 3 ሰዓት፣ በኢትዮጵያ አቆጣጠር፣ ወደ አገር ቤት የሚሰራጭ ሲሆን፣ ፍኖተ ህብረት ደግሞ ከ2 ሰዓት እስከ 3 ሰዓት፣ በዚሁ አገር አቆጣጣር፣ በዲሲ እና ባካባቢዋ ለሚገኙ ኗሪዎች የሚተላለፍ ሬድዮ ነዉ። ሁለቱም ሬዲዮኖች ስለአገራችን ተጨባጭ ሁኔታዎች ወቅታዊ የሆነ መረጃ በማቅረብ ይታወቃሉ ።




ድርጅትዎን በኢትዮጵያ ጋዜጣ ያስተዋውቁ!
(202) 291 4217

መኪናዎ ከተበላሸብዎት የሚጠግንልዎ አስተማማኝ ሜካኒክ መፈለግዎ አይቀርም:: በመሆኑም ብዙም ሳይቸገሩ መፍትሄ የሚሰጥዎትን በሙያዉ የታወቀ ሜካኒክ በስልክ ቁ. 301-979-0022 ደውለው አሁኑኑ ያነጋግሩ::

## መፍትሔው ምንድን ነው?

ወያኔ፣ የሙስሊሙን የቆየ ሀይማኖት በሌላ አልአባሽ በሚባል መጤ ሀይማኖት ለመቀየር እያደረገ ያለውን ጥረት ተከትሎ በወያኔ እና በሙስሊሙ ምዕመናን መካከል ያለው ውጥረት ወደ ግጭት ደረጃ ከፍ ማለቱ የሚታወቅ ሲሆን፣ በአዲስ አበባና በተለያዩ የአገሪቱ ክልሎች ወያኔ በወሰዳቸው ወታደራዊ እመቃዎች በርካታ ሙስሊሞች ለከፍተኛ የአካል ጉዳት፣ ለሞት እንዲሁም ለእስር ተዳርገዋል::

ይህንንኑ የወያኔ አረመኔያዊ ድርጊት በመቃወም እዚህ አሜሪካ፣ ዋሽንግተን ዲሲ በሚገኘው ስቴት ዲፓርትመንት ፊት ለፊት፣ በዋሽንግተን እና አካባቢው የሚገኙ ሙስሊሙች ሀሙስ ነሀሴ 2/2012 የተቃውሞ ሰልፍ አድርገዋል::





በዚህ የተቃውሞ ሰልፍ ላይ እጅግ በርካታ ሙስሊም ኢትዮጵያውያን የተገኙ ሲሆን፣ በተለይ የወጣት ሙስሊም ሴቶች ቁጥር ከማንኛውም ጊዜ ይልቅ አይሎ መገኘቱ የሁኔታውን ክብደት አመልካች ነው ሲሉ ብዙዎች አስተያየታችውን ይሰጣሉ::በሌላም በኩል ክርስቲያኑ ማህበረሰብ በሰላማዊ ሰልፉ ላይ በመገኘት፣ ወያኔ እንደሚለው ሳይሆን፣ ከሙስሊሙ ማህበረሰብ ጋር ያለውን ወንድማዊ አንድንት አሳይቷል::

በሰላማዊ ሰልፉ ላይ ሰልፈኛው በርካታ መፈክሮችን አንግቦ የታዩ ሲሆን፣ ከነዚሁ ውስጥ ጎልተው የተደመጡት፣ ስምንቱ የመፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴ አባላት እንዲፈቱ የሚጠይቀው እና የአሜሪካዉ ፕሬዚድዳንት ኦባማ፣የወያኔን አምባገነን መንግሥት እንዳይደግፉ ጥሪ የሚያቀርቡት መፈክሮች ነበሩ ።

በሰሜን አሜሪካ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ጳጳስ የሆኑት አቡነ ፊሊፖስ በዕለቱ በስፍራው በመገኘት እንደተለመደው ክርስቲያኑ ከሙስሊሙ ጋር ምንም አይነት ልዩነት እንደሌለው ይልቁንም ወንድማማች መሆናቸውን በስፍራው ከነበሩ ሙስሊሞች ጋር እጅ ለእጅ በመያያዝ ያላቸውን አጋርነት አሳይተዋል:: አቡነ ፊሊፖስ በጁላይ 1/2012 በዳላስ ቴክሳስ ሙስሊሙና ክርስቲያኑ በጋራ ባደረጉት ስብሰባ ላይ ተገኝተው ንግግር እንዳደረጉት ሁሉ፣ በዚህም ሰላማዊ ሰልፍ ላይ ተመሳሳይ አንድምታ ያለው መልእክት አስተላልፈዋል:: እንደ አቡኑ ንግግር ከሆነ፣ ሙስሊሙ እና ክርስቲያኑ ለረጅም ዘመናት ተከባብረው የኖሩ መሆናቸውን፤ ላለፉት 21 አመታት "የሀይማኖት ነጻነት ይከበር ወያኔ ጣልቃ መግባቱን ያቁም" እያሉ ሁለቱም ሀይማኖቶች ሲጠይቁ መቆየታቸውን፣ወያኔ በሙስሊሙ እምነት ላይ ችግር እንደፈጠረ ሁሉ፣ በክርስቲያኑ ላይም ተመሳሳይ ጥቃት እያደረሰ መቆየቱን፤ አሁንም ቢሆን ሙስሊሙ ያለው ሀይማኖቴ ይከበርልኝ እንጂ ሌላ ጥያቄ እንደሌለው፤በሙስሊሙ ላይ የሚደርሰው አፈና ከቀጠለ ሌላ ነገር ሊከተል እንደሚችል፤ ሀይማኖት የሌለው ወያኔ እራሱ እያሸበረ ሙስሊሙን አሸባሪ ማለቱ ተቀባይነት እንደሌለው እና ወያኔ ሙስሊሙን እና ክርስቲያኑን ለማጥፋት የተነሳ ስለሆነ መፍትሔው ምንድን ነው? ሲሉ ጥያቄ አቅርበዋል::


ገጽ 3

## ዝግጅቱ በእጅጉ የተሳካ ነበር

ኢሕአፓ ወክንድ

ኢወክንድ ቅዳሜ ጁላይ 14/2012 ፣ ኢወክንድን ለማጠናከር በሚል ታላቅ የእራት እና የመዝናኛ ምሽት ማድረጉን ለማወቅ ተችሏል::

ዋሽንግተን ዲሲ ፤ አስራ ስድስትኛው መንገድ ላይ በሚገኘው እ ኤቲካል ሶሳይቲ በሚሰኘው የመሰብሰቢያ አዳራሽ ውስጥ በተከናወነዉ በዚሁ የእራት እና የመዝናኛ ዝግጅት ላይ ከአሜሪካ የተለያዩ ግዛቶች፣ ከካናዳ እንዲሁም ከዲሲና አካባቢው የመጡ እንግዶችን ጨምሮ ሌሎችም በርካታ ተጋባዥ እንግዶች መገኘታቸውን ለማረጋገጥ ችለናል።





በዝግጅቱ ላይ፣ አጠር ያለ ድራማ ፣ ታዳሚውን ያሰድነቀ የእስክስታ ጭፈራ ፣ከፍተኛ ፉክክር የታየበት የጨረታ ስነ-ሥርዓት ፣ በመድረከ የተነበቡ ግጥሞች፣ ባህላዊ ዘፈኖች እና ሌሎችም ክንዉኖች የተካተቱ ሲሆን ለምሽቱም ከፍተኛ ድምቀት አቀዳጅተዉታል።

ሥነ-ስርዓቱ የተጀመርው በእራት ግብዣ ሲሆን፣ ከእራት ግቡብዣው በኋላ ፣ የኢወክንድ ወጣቶች ያዘጋጁት አጠር ያለ ድራማ መድረኩ ላይ ቀርቦ ታዳሚውን አዝናንቷል:: በዚሁ ድራማ ፤ ላይ አንጋፋዋ አርቲስት ጠለላ ከበደ ከኢወክንድ ወጣቶች ጋር በትወና ያደረገችዉ ተሳትፎ ትእይንቱን ማራኪ አድርጎታል ።

ከዚህ በኋላ፣ በዝግጅቱ ላይ ለመገኘት ከካናዳ ድረስ ተጉዛ የመጣችው ወጣት ገጣሚ፣ ምሳሌ አሊ ወደመድረኩ በመዉጣት የበኩሏን አጠር ያለ ንግግር ካደረገች በኋላ መድረኩን ለአባቷ፣ ለተወድጁ ገጣሚ ለአሊ ሁሴን ለቃለች:: አቶ አሊም ቢሆን ከዛው ከካናዳ ዊንፔግ ከተማ ድረስ ኢወክንድ ባዘጋጀው የእራት ግብዣ ላይ ለመገኘት እዚህ አሜሪካ ድረስ የመጣ ሲሆን፣ በእለቱም ከመድረኩ ላይ ከአንዴም ሁለት ጊዜ በመገኘት ታዳሚውን ዘና ያደረጉ አጠር ያሉ ንግግሮችን ከማድረጉም በተጨማሪ ተወዳጅ ግጥሞቹን በማንበብ ታዳሚውን አስደስቷል:: አቶ አሊ የዛሬ ዓመት በተመሳሳይ ዝግጅት ላይ መገኘቱ የሚታወስ ሲሆን፣ እንዲህ ባሉ መድረኮች ላይ ብቅ በማለት ተወዳጅ ግጥሞቹን በማሰማት የታወቀ ገጣሚ ነው::

በዚሁ እለት፣ ለዝግጅቱ ልዩ የሆነ ድምቀት የሰጠው ሌላ ነገር ፣ለጨረታ የቀረበዉ የአጼ ቴዎድሮስ ምስል ነበር:: በዚሁ የጨረታ ስነስርአት ላይ ታዳሚው የቋራዉን አንበሳ ምስል የራሱ ለማድረግ በየግሉ ያደረገው ፉክክር እጅግ አስደሳች ነበር:: ምስሉን የዲሲ ኗሪዎች ለማስቀረት ያደረጉት ጥረት ሳይሳካላቸው ቀርቶ፣ ከሲያትል የመጡ እንግዶች የጨረታው አሸናፊ በመሆን የአጼ ቴዎድሮስን ምስል የራሳቸው ለማድረግ በቅተዋል::

ለዚህ ኢወክንድ ላዘጋጀው የእራት ምሽት ልዩ ድምቀት የሰጠው ተጨማሪ ነገር ቢኖር በዕለቱ የቀረበው የባህል ጨዋታ ነበር:: የባህል ጨዋታውን ተከትሎ በመድረኩ ላይ እስክስታ ይወርዱ ከነበሩት፣ ተወዛዋዦች መሀል አንዱ ጥቁር አሜሪካዊ መሆኑ ታዳሚውን በእጅጉ አስደንቋል:: አሜሪካዊዉ ያሳይ የነበረው የእስክስታ ትእይንት፣ ገጽ 8

ዘረኛው ወያኔ፤ በኃያላኑ መንግሥታት አይዞህ ባይነትና ድጋፍ ታግዞ ፤ በወርሐ ግንቦት 1983 ዓ.ም አዲስ አበባን ያዘ ። በጊዜዉ ደበብዊዉንና ደበብ ምስራቃዊዉን የኢትዮጵያ ግዛቶች ገና ያልተቆጣጠረ እንደመሆኑ ሌሎች ዘመቻዎች ይጠብቁት ነበር ። ከዚህ ይልቅ ፤ ተከዜን ከተሻገረ በኋላ ባደረገዉ ግስጋሴ ወደኋላ ጥሎት በመጣዉ ሰሜናዊ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍል ዉስጥ ሳይጠናቀቅ የሚጠብቀዉ ሥራ መኖሩ ወያኔን በይበልጥ የሚያሳስበዉ ጉዳይ ነበር ።

በዚህ አገራዊ ክፍል ዘርና ጎሳ ሳይለዩ ለሕዝብ እኩልነት ፤ለማህበራዊ ፍትህና ለሀገር አንድነት ታጥቀዉ የሚታገሉ የሕዝብ ልጆችን ያሰለፈዉ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ሠራዊት (ኢሕአሠ) ይንቀሳቀስበታል ።የዚህ ሠራዊት ህልዉና ደግሞ ለወደፊቱ በኢትዮጵያ ላይ ሊተገበረዉ ካቀደዉ ዘረኛ ፖሊሲና የጎሳ ክልል ሸንሸና አንጻር የሚኖረዉ አንድምታ ለሥልጣን መደላድሉ ከቶ የማይበጅ መሆኑን ወያኔ ጠንቅቆ ተረድቶታል ። የኢሕአፓ /ኢሕአሠ ታጋዮች "ታላቋን ኢትዮጵያ" ለመፍጠር የነበራቸዉ ዉጥን ራዕይ የጦር በለስ የሰመረለት የወያኔዉ ዘረኛ ቡድን በቀትር የሚባንንበት ቅዠት ነበር ።
በመሆኑም የሱዳንንና የሻዕቢያን ተዋጊዎች አቀናጅቶ በማሰለፍ በጎጃምና በጎንደር ክፍላተ ሀገር የከበባ ወረራዉን ጀመረ። በተከታታይ በተደረጉ ዉጊያዎች በርካታ የኢሕአሠ /ኢሕአፓ ታጋዮች ተሰዉተዋል ። በሰኔ 1983 ዓ.ም በጎንደር ክፍለ ሀገር በቋራ ወረዳ ዉስጥ ሳንኪሳ ተብሎ በሚጠራዉ ስፍራ በኢሕአሠ ኃይል ላይ በተከፈተዉ የማጥቃት ዉጊያ ላይ ጸጋዬ ገብረ መድሕንን ጨምሮ የኢሕአፓ ከፍተኛ የአመራር አባሎች በወያኔ እጅ ወድቀዋል።ከነዚሁ መሀከል በለጠ አምሃ ፤ ስጦታዉ ሁሴን ፤ ይስሃቅ ደብረ ጽዮን ፤ ተክላይ ገብረ ሥላሴ ፤ሃጎስ በዛብህ፤ አዛናዉ ደምሌ ይገኙበታል ።

እነሆ እነዚህ አይበገሬ የሕዝብ ልጆች ከዘረኛዉ ወያኔ ደይን ከተጣሉ ሃያ አንድ ዓመታት ተቆጥረዋል ። በተያዙበት ሰሞን ባሕር ዳር ዉስጥ ከመታየታቸዉ በቀር ከዚያ ወዲህ መዳረሻቸዉ እስከዛሬ አልታወቀም ።ከአፍላዉ ዕድሜአቸዉ አንስቶ ለሚወዷት ሀገርና ከአብራኩ ለተከፈሉለት ሕዝብ እኩልነትና ነጻነት ሲታገሉ ከጠላት እጅ ስለወደቁት ስለነዚህ ጀግኖች ዕጣ ፈንታ አንድም አለም አቀፍ የሰብዐዊ መብት ተቆርቋሪ ድርጅት ሲሟገት አልተደመጠም ። የዜጎች ሰብዐዊ ክብርና መብት ጉዳዮችን ነዉ ብለዉ የሚለፍፉ ብሔራዊ ተቋማት እንኳ ( ከኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ በስተቀር ) በዚህ ጉዳይ ላይ ጩኸታቸዉን ያሰሙበት አንድም ወቅት አልተመዘገበም ።

ጓደኞቹና የትግል ጓዶቹ "ደብተራዉ" በሚል ቅጽል ስም ይጠሩታል ።ለማጠናቀቅ ከሁለት አሥርት ዓመታት በላይ በሚወስደዉና በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስትያን ትዉፊታዊ ትምህርት ለበቁቱ ሊቃዉንት ብቻ የሚሰጠዉን ይህን ታላቅ ማዕረግ በስሙ ላይ ደርበዉ መጥራታቸዉ ያለምክንያት አልነበረም ። የልጅነት አስተዳደጉ በቀድሞዉ የሸዋ ክፍለ ሀገር በሚገኘዉ የዝቋላ አቦ ገዳም ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ፤ በቤተ ክህነት ትምህርቱ ገፍቶበት ቅኔና አቋቋምን ለመማር በቅቷል ።

በአዲስ አበባዉ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ማህበር ጥላ ስር ታገል/ ስትራግል በሚል ርዕስ በአማርኛና በእንግሊዘኛ ቋንቋ ይታተም የነበረዉን የወቅቱን ዝነኛ ጋዜጣ ሳነበበ ጸጋዬ የታደለዉን የተባ የብዕር ሰዉነት ማስተዋል አይገድደዉም ።

# ትላንትና

## 21 ዓመታት በወያኔ እስር ቤት

ደብተራዉ ከቀዳሚዎቹ የማህበሩ መስራቾችና ከጋዜጣዉ ህትመት ጀማሪዎች አንዱ ከመሆኑም በላይ በተለይ የጋዜጣዉ የአማርኛ ክፍል አዘጋጅ ነበር ።በወቅቱ በዚሁ ጋዜጣ ላይ ያወጣቸዉ በነበሩ ጽሁፎች ላይም ጸጋዬ ገብረ መድሕን የሚለዉን ስም ነበር የሚጠቀመዉ ።

የዚያኔዎቹ የዩኒቨርስቲዉ ተማሪዎች የሥነጽሁፍ ችሎታቸዉን ከሚፈትሹባቸዉ መድረኮች መሀከል በየዓመቱ በልደት አዳራሽ ይካሄድ የነበረዉ የግጥምና የዲስኩር ዉድድር ይገኙበታል። የኃይሉ ገብረ ዮሐንስን (ገሞራዉ ) "በረከተ መርገም" እና የዮሐንስ አድማሱን "የገደል ስር አጥንት" የመሳሰሉ ግጥሞች ዉበትንና ማህበረሰባዊዉን ቁጣ አዋህደዉ በንባብ በተዥጎደጎዱበት በዚያ መድረክ ላይ ቀርበዉ ከተደራስያኑ ይበልታን ከተቀዳጁት ምርጥ ሥራዎች ጎን ለጎን የሚከተለዉ የደብተራዉ " ዘዉዱን ገልብጬ በነበረ" የሚጠቀስ ነዉ ።

ቁማር ጨዋታ ተጫዉቼ
አፌጩብጭቤ ቀረሁ--ተረትቼ
ምነዉ ዕድሌ በሰመረ
ዘዉዱን ገልብጬ በነበረ ፤1
ጸጋዬ ገብረ መድሕን በዚህ ግጥሙ ታላቅ የቅኔ አዋቂነቱን አንጸባርቆበታል። ይህ ብቻም አይደል ፤ ገና አዉጥቶበታል ። የሚቀጥለዉንም ግጥሙን ስንመረምር የምንደርስበት መደምደሚያ፤ከመጠቀ የአማርኛ ቋንቋ ችሎታዉ ወዲያ ፤ ጸጋዬ ገና ከጠዋቱ ራሱን ከብዙኃኑ ሕዝብ ዕጣ ፈንታ ጋር ያቆራኘ ባለቅኔ መሆኑን የሚያመለክት ነዉ ።

ነፎ መስዬ አበያ
ባዶ እጄን ቆሜ ገበያ
አንገበገበኝ ንዴቱ
ሲሸጥ ሲለወጥ ማየቱ
ብዙዉ በርካታዉ በጥቂቱ፤2

ባለቅኔዉ ጸጋዬ ፤ዘመናዊዉን የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን አዲስ አበባ ከተማ ዉስጥ በቅዱስ ዮሴፍ ትምህርት ቤት ተከታትሏል ።በዚሁ ት/ቤት በተማሪነት በቆየበት ጊዜ በነበረዉ ልዩ የቋንቋ ችሎታ ሳቢያ ለተቀሩት ተማሪዎች የአማርኛ መምህር በመሆን ሠርቷል ። ከዚያ በኋላም ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርስቲ በቋንቋ ትምህርት የመጀመሪያ ድግሪዉን ያገኘ ሲሆን በተለያዩ ሥፍራዎችም በመምህርነት አገልግሏል ።
ጸጋዬ በዩኒቨርስቲዉ ቆይታዉ ወቅት በተማሪዎች የለዉጥ እንቅስቃሴ ዉስጥ ግምባር ቀደም ድርሻ አበርክቷል ።በኢትዮጵያዉያን አቆጣጠር ጥር 1959 ዓ.ም የአዲስ አበባውን የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ማህበር ( አአዩተማ ) ለህልዉና ካበቁት መስራች ታጋዮች አንዱ ከመሆኑም በላይ ማሕበሩ ያደረጋቸዉን እንቅስቃሴዎች በቆራጥነት መርቷል ። የተማሪዉ ትግል ተጠናክሮ ሥር ነቀል መስመር እንዲይዝ በማድረጉ ጥረት ዉስጥ ጥላሁን ግዛዉን፤ ዋለልኝ መኮንንን ፤ ጸሎተ ሕዝቅያስን ፤ ዮሃንስ ብርሃኔን ፤ ወዘተ... ከመሳሰሉት ታጋዮች ጋር በመሆን ጸጋዬ የከፈለዉ ድርሻ የላቀ ነዉ ። በዚሁም ሳቢያ በተለያዩ ጊዜያት በነበረዉ መንግሥት የጸጥታ ኃይሎች ታድኖ እየተያዘ እስራትና ስቃይ ደርሶበታል ።

ገጽ 7

# ኢሕአፓ

## 40 ዓመታት በትግል ጎዳና

በ1960ዎቹ ዓመታት የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ እያደር ተጠናክሮ የፖለቲካ ትግል መስመር እያገኘ ሄደ ። የአጼ ኃይለሥላሴ መንግሥትና ባላባታዊዉ ሥርዓት ለአገሪቱ እድገት ማነቆ መሆናቸዉ በአብዛኛዎቹ የንቅናቄዉ ተሳታፊዎች ዘንድ ታምኖበታል ።መፍትሔ ፍለጋ በሚደረጉ ዉይይቶች ፤ከጥገናዊ ለዉጥ እስከ ሥር ነቀል አብዮት ያሉ ተቃራኒ አስተሳሰቦች መብላላት ጀምረዉ ነበር ።የኋላ ኋላ እንደሚታየዉም ተመሳሳይ ሃሳቦች እየተሳሳቡ በዓላማ ወደመቧደን ደረጃ ተመነደጉ።
ከዚሁ የተማሪዎች ንቅናቄና በመላዉ ዓለም ተሰራጭተዉ ከነበሩ ሥር ነቀል አስተሳሰብ የነበራቸዉ ምሁራን ፤ ላባደሮችና አርሶ አደሮች እንቅስቃሴ አብራክ ነዉ እንግዲህ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ-ኢሕአፓ ፤ (በዉጥን መጠሪያዉ ኢሕአድ) ተፈጥሮ በሀገራችን ታሪክ ላይ የራሱን አሻራ የሚያሳርፍ ተግባሩን የሚያያዘዉ ።

በሥሩ አዕላፋት ኢትዮጵያዉያን/ ኢትዮጵያዉያትን በእኩል አሰልፎ አታግሏል ። ከጎሳና ከዘር ክፍፍል አባዜ የጸዳ ፤ ከራስ ካሳር እስከ ሞያሌ ፤ ከጋምቤላ እስከ ፈርፈር ከሚዘረጋዉ የአገሪቱ ምድር የፈለቁትን ታጋዮች ለአንድ አገራዊ ራዕይ ያሰለፈ ታላቅ ድርጅት ለመሆን በቅቷል ። በአፈጣጠር ዕድሜዉ ከሌሎቹ ሀገርኛ የፖለቲካ ቡድኖች አይቀድምም ። መነሻና መድረሻዉን ጠንቅቆ በተገነዘበ ዘመናዊ የፖለቲካ ድርጅትነቱ ግና ፋና ወጊ ነዉ። በአመለካከት ጥልቀትና በዓላማ ጥራት ፤ እንዲሁም ለሥነስርዓት ባላቸዉ ተገዢነት ከጠላት ዘንድ ሳይቀር አድናቆትን ያተረፉ አባላቱን በማነጽ ረገድም በኩር ነዉ ። የጽናትና የአይበገሬነት መለኪያ ፤ከሕዝብ ክብርና ከኢትዮጵያ ፍቅር አንጻር ሞትና ስቃይ ኢምንት መሆናቸዉን ባስመሰከሩ አባላቱ ግብር ሁሌም የሚወደስ ድርጅት ነዉ -ኢሕአፓ። በሚያራምደዉ ርዕዮተ ዓለምና በድርጅታዊ ፕሮግራም ረገድ ብዙ ተለዉጧል ፤ ሕዝቡን የሥልጣን ባለቤት ለማድረግ ከገባዉ ቃል ኪዳንና ለማንም ከማያንበድድ ጥብቅ አቋሙ አንጻር ግና ኢሕአፓ ከነበረበት አለ።

ገጽ 7

ከዚህ ቀደም ምዕራባዊያን በተለይም የአሜሪካ መንግስት የኢትዮጵያን ሕዝብ የለውጥ ምኞት አፈር እንዳበላው ሁሉ ዛሬም በካህዲዎችና ባንዳዎች ተጠቅሞ የመሰረታዊ ለውጥ ዕድላችንን ሊያደባይ ተነስቷል:: ጆሮ ያለው ይስማ! ነውና ሀገራችን እንደገና በጨቋኞች መገዛቷ እንዲቀጥል ከቶም ልንፈቅደው ልናደርገው የሚገባ አይደለምና::

ወደኋላ መለስ ብለን ታሪክን ስንቃኝ የኢትዮጵያ ሕዝብ የጣሊያንን ወራሪ ጦር ሊቋቋም ሲነሳ ምዕርባውያን በጦርና ጋሻ የሙሶሎኒን ዘመናዊ ተብዬ ሀይል ለመጋተር ተነሳ ብለው ሲሳለቁ እንደነበር አንረሳም:: የኢትዮጵያ አርበኞች የአጼውን አገዛዝ አንፈልግም፤ ሪፑብሊክ እንመስርታለን ወዘተ ብለው ሲነሱም እንግሊዝ አጼውን በጉልበት በራሳቸው ላይ አምጥቶ እንደጫነና የጥቁር አንበሳ ታጋዮችንም እንዳፈነና እንዳሳፈነ፤ እነ በላይ ዘለቀንም እንዳሰቀለ፤ እነ ደጃዝማች ታከለ ወልደ ሐዋርያትንም እንዳስገለለ የሚታወቅ ነው:: የዛሬው ትውልድ ይህን ሁሉ መማርና ማወቅ አለበት:: የአጼውን ስርአት አሜሪካ ደግፎና አቅፎ አቆይቶታል::

በ 1953 ዓ.ም እነ መንግስቱ እና ገርማሜ ንዋይ ጨቋኙን ሥርዓት ሊፈነቅሉ ሲነሱ ይህን ሙከራ በማክሸፍ አሜሪካ ግንባር ቀደም ሚና ነበራት:: የኢትዮጵያን ተማሪዎች እንቅስቃሴ በሀገር ውስጥም በውጭም ለማደናቀፍ አሜሪካ የተቻላትን ሁሉ አድርጋለች::

ይህ ታሪክ ነው፤ ሀቅ ነው:: የደርግ አገዛዝን የሶቭየት ህብረት አጋርና ኮሙኒስት በሚልም አሜሪካ በአንድ በኩል ለዕቅድ የማይመች ሀገር ወዳድ ነው ብላ አህአፓን እያስጠቃች በሌላ ዘርፍ ደግሞ ከእንግሊዝ፤ ስውዲንና ኖርዌይ በተለይ ከገንጣዮችና ቅጥረኞች በማበር ኢትዮጵያን እንደአገር አጥቅታለች:: በረሀቡ ሽፋን ወያኔን ያስታጠቀችው አሜሪካ ናት:: ልገንጠል ባዩን አነግን ሲረዱና ሲደግፉ የነበሩት እንግሊዞች እና ጀርመኖች ናቸው:: ሩሲያ ለደርግ እርዳታ መስጠትዋን እንድታቆም አድርጋ ለወያኔ ሁኔታውን ያመቻቸችው አሜሪካ ናት ፈረንሳይና ጣሊያን ለወያኔና ለሻዕቢያ የማያመች የሽግግር አማራጭ ሲያቀርቡ አይሆንም ባይ አሜሪካ ነበረች:: አሜሪካ ዋናው ፍላጎቷ የኢትዮጵያ አይሁድ የተባሉትን ቤተ እስራኤሎችን ማውጣት ነበርና በሀገራችን ላይ ለሚመጣው አደጋ ደንታ አልነበራትም:: በሱዳን በኩል ኦፕሬሽን ሞሰስ በተባለው ከተባበሯት ወያኔዎች ጋር መተቃቀፉ ደስታዋ ነበር:: ይህን በተመለከተ በአማርኛ ተተርጉሞ ያለውን ኦፕሬሽን ሰለሞን የሚለውን መጽሐፍ ያነቧል:: ዜጎችን ሸጠው የከበሩ ዛሬም አሉ፤ ዛሬም ዜጎችን ለባዕድ ሊሸጡ እየተራወጡ ናቸው:: የመንግሥቱ ኃይለማሪያም ውድቀት እየቀረበና ግልጽ እየሆነ ሲመጣም ኢህአፓ ከቋራ ሲያስተላልፈዉ በነበረው የፍኖተ ዴሞክራሲ ራዲዮ ሕዝብን አደጋ መጥቷል ብሎ አስጠነቀቀ:: የወያኔን የገንጣዮችን እንዲሁም የባእዳንን ሴራ በሰፊው አጋልጦ ሕዝብ ነቅቶ እንዲጠብቅ፤ እንዲደራጅ፤ በኅበዝ አለቃዎቹም ዙሪያ በገጠር ለትግል እንዲሰባሰብ ጥሪ አደረገ:: ይህን ጥሪ ያዳመጡ ወጣቶችና ተማሪዎች ወያኔ አዲስ አበባ ሲገባ በተቃውሞ ሲሰለፉና ሲሰው ክህደት ልምዱ ያሉ ምሁሮች ደግሞ ከመለስ ጋር ተቃቀፉ፤ ጊዜ ይሰጣቸው ወዘተ በሚል የማደንዘዣ መርዛቸውን ረጩ::

ጆሮ ያለው ይስማ ህሊና ያለው ያስታውስ!

# ነጻ ሀሳብ

## የአሜሪካ ትእዛዝ ወይስ የሕዝባችን ውሳኔ?

## ጆሮ ያለው ይስማ! ዓይን ያለው ይይ! ሀገራችን ዳግም ለቅርጫ ቀርባለችና

በእንግሊዝ ሀገር በለንደን ከተማ በተካሄደው የሽግግር ጉባኤ ተብዬ ላይ የታሪካዊቱን ኢትዮጵያ ዕጣ አንድ አሜሪካዊ ኮህን ተብዬ ባለሥልጣን ብጣቂ ወረቀት ጽፎ መወሰኑ ዘላለማዊ ምጸታችን ነው:: ኮህን ወይ አሜሪካ የዚያን ጊዜ ዋና ጭንቀታቸው ቤተ እስራኤሎቹን ማውጣት ነበርና ( ለዚህም ኮህን በብዙ ተሸልሞበታል) ስለ ኢትዮጵያ የነገ ሁኔታ ጉዳያቸው አልነበረም:: በዚህ ጉባኤ ተብዬ ለይስሙላ ወይም ራሱ የአነጉ ዋና መሪ እንዳለው በግድግዳ ዝንበነት ወይም በአጃቢነት አነግ ቢገኝም ኮህን ከወያኔና ከሻዕቢያ ተመካክሮ የወሰነው ወያኔ አዲስ አበባ ሳይገባ ይቆጣጠር፤ ሻዕቢያ አስመራን ይያዝ ይገንጠል የሚል ነበር:: አሜሪካ የኢትዮጵያን መገነጣጠል መቸም አትደገፍም ይሉ የነበሩ በጊዘው መርዶአቸውን አግኝተዋል:: ዛሬም በሀገራችን ላይ አሜሪካ መርገም ልታወርድ ተነስታለች::

ወያኔን ደግፋና አቅፋ ለስልጣን ካበቃች በኋላ አሜሪካ የመለስ አገዛዝ እንዳይነካ ያደረገችው ትግልና በተለይም የኢህአፓን ጸረ ወያኔ ትግል በአፍሪካ ቀንድና በምስራቅ አፍሪቃ ለማደናቀፍ ያደረገችው ጥረት ቀላል አልነበረም:: አሜሪካ ሀይሏን ተጠቅማ ድጋፍ ባትሰጣቸው ኖሮ ወያኔም ለስልጣን ሻዕቢያም ለግንጠላ አይደርሱም ነበር:: ያኔም ነገር ተበላሽቷል ብሎ ኢህአፓ ሲጮህ ሰሚ ጠፍቶ ለሰዎቹ ጊዜ እንስጥ በሚል ስንቶች ሲለፍፉና ወያኔን ሲደግፉ የታዘብነው ነው:: ቀውጢ ቀን ሲመጣ ከወያኔ ተጣላን ያሉት ወገኖች ከወያኔዎች ሊታረቁ ኮሚቴ ማቋቋማቸው የሚዘነጋ አይደለም:: የአደባባይ ንትርክ መሰል አቅዋማቸው ለየዋሆች የተቃኘ ነው::

ወያኔዎች ዘረኞች ናቸውና ለውጡ የሚያጠቃቸው እስከመሰላቸው ድረስ መተጅባበራቸው አይቀሬ ነው:: ዘር ከልጓም ይጠቅሳል ማለቱ ቢቀፍም ለጉዶቹ ይሰራል::ጸረ ወያኔ ነን ባዮቹን በዮኒቨርስቲው ወሽቆ አስተማሪዎች አሜሪካና እንግሊዝ ናቸው:: ለቀጣይ ክህደት እያዘጋጁቸው መሆኑ ምስጢር አይደለም:: ለጥቆም የኤርትራ የግንጠላ ሂደት በካህዲው መለስ ድጋፍ ሊጠናቀቅ ሲጥር የአፍሪካ ሀገር ተወካዮችን በተባበሩት መንግስታት ጫና አድርጎና አስፈራርቶ ግንጠላውን ደገፉ ያለው በቅድሚያ አሜሪካ ነው:: ስንቱስ ተወርቶ ያበቃል!

ወያኔን ከውድቀት ያዳነው አሜሪካ ነው--ቅጥረኞቹን በመጠቀም::

እንግሊዝም በአቅሟ ሚና ነበራት:: ባዕዳኖቹ ብቻቸውን አልነበሩም--ዋናውን የሰሩት ሀገር በቀል ከሀዲዎችና ባንዳዎች ነበሩ:: በ1997ቱ ምርጫ ጊዜ የህዝብን ወሳኝ ትግል የቀበሩት ተቃዋሚ ነን ያሉት መሪዎች ነበሩ:: ታሪካዊ እንደምታና ሚዛን ይኖረው የነበረውን የሙት ከተማ አድማ ከአሜሪካ ኤምባሲዋ ተጠሪ ቪኪ ህደልሰተን ጋር አብረው ካከሸፉት ከሀዲዎች አንዱ ለአዲስ ጸረ ሕዝብ ተልእኮ ወደ አሜሪካ ተልኮ ገብቷል:: ያን ወሳኝ ትግላል አክሽፈው ከወያኔ ጋር ሊደራደሩ የተሰለፉት የባእድ ቅጥረኖች የሕዝብን የለውጥ ዕድልና ተስፋ ገድለዋል:: በዚያውም አፍረውና አጥፉን ብለው መሰወር ሲገባቸው ዛሬም አለን ብለው እንደገና የህዝብን የለውጥ ትግል ለማክሸፍ የባእዳን ቅጥረኛ ሆነው መወራጨቱን ተያይዘውታል:: ለዛሬው የተሰጡአቸው ተልዕኮ ደግሞ የህዝብ ትግል ከተፋፋመ፤ በግበጽ፤ በቱኒዚያ፤ በየመን ወዘተ ደረጃ የሕዝብ ትግል ከቀጠለ ወያኔ ይፈጃልና ሌላ መፍትሄ እንፍልግን እንዲሰብኩ ነው:: በዚህም መሰረት አብዮት፤ መሰረታዊና ሥር ነቀል ለውጥ ብሎ መነሳቱ ሀገርን ይጎዳልና ይልቅስ ከወያኔ ሀገር ወዳዶች እንተባበር፤ ለሚቀጥለው ምርጫ እንዘጋጅ ብለው ቅሌታም አድርባይነትን እንዲለፍፉ ታዘው እያቀረሹ ናቸው:: አብዮት ሀገር ይጎዳል፤ መሰረታዊ ለውጥ ሀገር ይጎዳል ብሎ ከመለፈፍ ሌላ ምን ደረጃ ዓሳፋሪነትና፤ ቡክንነትና ክህደትስ ይጠብቃል::

ዛሬ ባዕዳን የተመጠነልን ሴራ የባዕድ ቅጥረኞችን በሞላ በጋራ አሰልፎ በወያኔ ግም ጫማ ስር የሚደፋ ነው:: መለስ ኖረ አልኖረ የወያኔ አዛገች እሽ ካሉ ከመለስ ተጣሉ እንጂ ከወ ያኔነት ያልራቁት የቀድሞ ተብዬ ወያኔዎችን በከሀዲ ባንዳዎች አጅቦ የስልጣን ተጋሪ ለማድረግ እየተሞከረ ነው:: ሞኝ በህልሙ ቅቤ ባይጠጣ ብንል አይፈረድብንም:: አገዛዙ በቀድሞው መልክ ሊገዛ በማይችልበት ሁኔታ ገብቷል:: ሕዝብም እምቢኝ አሻፈረኝ ማለቱን ግልጽ እያደረገ ነው:: ይህ ገዢ ነን ባዩን ቡድን ቢያስጨንቀውም ቡድኑን ለመከላከል በአሉባልታዎችና ሌላም ያለውን ቀጣይ አድርገውና ለውጥን ማለትም ስር ነቀል ለውጥን መሻት ጥፋትና ዕልቂትን ማቀንቀን ነው ብለው የሚለፍፉ መኖራቸውን ደግሞ የሚያሳይ ነው:: የመለስ አገዛዝ በአብዮት እና ስር ነቀል ለውጥ መወገድ አለበት ከዚህ ሌላ ይህን ኩሶ ማስወገጃ መንገድ ባለመኖሩ ነው:: ስር ነቀል ለውጥ ያፋጃል ብሎ መጮህ ለትዝብት ይዳርጋል:: አብዮት ወይስ መሰረታዊ ለውጥ ብለን ብንነሳ ወያኔ ይፈጀናል ብሎ መራመድ ለውርደት ይዳርጋል:: ወያኔ ለተባለው መርገም መድሀኒቱ ስር ነቀል ለውጥ ብቻ መሆኑ ግልጽ ነው:: ይህ ደግሞ መስዋዕትነትን መጠየቁ መታወቅ ያለበትም ነው:: ከታገልን ወያኔ ይገድለናልና ከወዲሁ እጅ እንስጥ ሰበካ ትላንት የህዝብን ለውጥ አምጪ አድማ አክሻፊዎች አቅዋም ነው:: ኢሕአፓ የሕዝብን አቅዋም አስቀድሞ በመገኘቱና ለክህደት ስብስብ ተገዢ ባለመሆን ራሱን ይጎዳል፤ ይነጠላል ለሚለው መልስ ከህዝብ ጎን እስከተሰለፈ ድረስ ከባዕድ ሎሌዎች መነጠሉ የማያሳስበው አይደለም የሚል ነው:: የባዕድ ቅጥረኞች ዛሬ ጥምብ እንድዳየ ጇፌ አሞራ ሲሰባሰቡ እየታዩ ናቸው:: ዳግም ሀገርን ሕዝብን ሲክዱ:: አድርባይነታቸውን ህልው ሊያደርጉ:: ዜጎች ነቅተው በመገኘት ሴራቸውን ሊያወግዙ ይገባቸዋል:: የባዕድ ሴራ ይሳካል ብለው ሀገርን ለጎዱ የተነሱትን ማሳፈር የዜግነት ግዴታችን ነው:: ኢትዮጵያዊ ናቸው ተብለው ሊጠቁ የተነሱትንም እነ ኢሕአፓ'ንም መደገፍ አለብን:: የዘረኞቹንም ሴራ ማክሸፍ ያስፈልጋል:: ለሀገርና ለሕዝብ መቆም እንጂ ለባዕድ መስገድና ለባርነት ራስን መዳረግ ኢትዮጵያዊነት አይደለም:: ሕዝባችን መሰረታዊ ለውጥን፤ በወያኔ መወገድን፤ የዘረኞቹን መውደምን ይፈልጋል:: አሜሪካና ባዕዳን፤ ባንዶችና ከሀዲዎች ደግሞ ወያኔን ጠግነው የወያኔን አገዛዝ እነሱን አቅፎ እንዲቀጥል ይፈልጋሉ:: አምርረን ከታገልን የአሜሪካም ሆነ የካሀዲዎች ፍላጎት ሳይሆን የህዝብ ምኞት የሚሳካ ይሆናል:: ኢሕአፓ ባለው አቅሙ ይህ እውን እንዲሆን ይታገላል::

ክህደት አሳፋሪ ነው!

ሕዝብ ሀያል ነው!

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!

# 21 አመታት...

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ )ን በአገር ቤት ከመሠረቱት ቀደምት አባላት ዉስጥ ጸጋዬ ገ/መድሕን አንዱ ነዉ ። ገና ከዉጥኑ የድርጅቱ መዋቅር በአገር ቤት እንዲዘረጋና እንዲጠናከር የበኩሉን አስተዋጽዖ አድርጓል ፤ ትግሉ የሚጠይቀዉንም መስዋዕት ግንባሩን ሳያጥፍ ከፍሏል ። ላለፉት ሠላሳ ዘጠኝ ዓመታት የድርጅቱ ልሳን ሆና ያገለገለችዉ "ዴሞክራሲያ" ጋዜጣ ሰኔ 1966 ዓ.ም ላይ ስትወጠን ከዶክተር ተስፋዬ ደበሳይና ከዮሐንስ ብርሃኔን ጋር የጋዜጣዉ ዝግጅት ቦርድ አባል በመሆን ሠርቷል ። በዚያ የድርጅቱ ሊጋ ዕድሜ የጋዜጣዉ ዝግጅት እጅግ ጥንቃቄ የሚያሻዉ ከመሆኑም በላይ አድካሚ ተግባር የነበረ በመሆኑ የተነሳ ሐላፊነቱ በዋዛ የሚሸከሙት አልነበረም ። ከጽሁፍና ከአርትኦት ሥራ በተደራቢ ለጋዜጣዉ ሕትመት ግብዐት የሚያስፈልጉትን ቁሳቁስ ገዝቶ የማቅረቡ ጣጣ በነርሱዉ ትከሻ ላይ የወደቀ ነበር ። ለደኅንነት ሲባል ሲደረግ ከነበረዉ ጥንቃቄ አንጻር ጋዜጣዉ የሚባዛበትን ሥፍራ መለዋወጥ የግድ ነበር። በዚህ ረገድ ራስ መኮንን ድልድይ አካባቢ በተለምዶዉ አጠራር "ቲ-ሩም" ተብሎ የሚታወቀዉ መዝናኛ ከሚገኝበት የአፓርታማ ህንጻ ላይና ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስትያን አካባቢ የሚገኙት ሁለት ጸጋዬ በስሙ የተከራያቸዉ ቤቶች ብዙዉን ጊዜ የጋዜጣዉ ጽሁፎች በዉድቅት ሌት የሚተየቡባቸዉ ነበሩ። በወቅቱ ሕዝባዊዉን ትግል በማቀጣጠሉ ተግባር ላይ ድርጅታዊዉን ርዕዮተ ዓለም በማስረጽ ረገድ "ዴሞክራሲያ" የነበራት ልዩ ሚናና በአንባቢዎቿ ዘንድ የነበራት ተወዳጅነት የዎስቱ ታጋዮች ብስለትና ሥነ ጽሁፋዊ ክሂል ድምር ዉጤት ነበር ማለት ይቻላል ።



ጸጋዬ ገብረ መድሕን አዲስ አበባ ሆኖ በህቡዕ ሲታገል ከቆዬ በኋላ በወቅቱ የትጥቅ ትግል በማድረግ ላይ ለነበረዉ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ሠራዊት (ኢሕአሠ ) የፖለቲካ ኃላፊ ሆኖ እንዲሠራ በመመደቡ ትግራይ ዉስጥ ወደሚገኘዉ አሲምባ አምርቷል ። ሠራዊቱን በመምራትና ሠራዊቱ በተፋለመባቸዉ በርካታ አዉደ ዉጊያዎች በመሳተፍ ለጓዶቹ ሁሉ የጠንካራ ታጋይነት አርአያ ለመሆን በቅቷል ። በአሲምባ የትጥቅ ትግል ላይ እያለም ለኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) የማዕከላዊ ኮሚቴ አባልነት የተመረጠ ሲሆን በጠላት እጅ እስከወደቀባት ቅጽበት ድረስ በዚሁ የሀላፊነት ደረጃ አገልግሏል ።

ጸጋዬ በትግሉ ጎራ የግንባር ሥጋ ሆኖ በግብር ካስቀረልን የአይበገሬነት፤ የመታመንና የጽናት ገድል ሌላ በሥነ ጽሁፋም ዘርፍ በርካታ ሥራዎችን ቸሮናል ።በዚህ አጭር ዜና ሕይወት መግቢያ ላይ ከሰፈሩት ቅኔዎቹ ሌላ "ናስተማስለኪ" ና "ግንባርከን አሳያቸዉ" የተሰኙት ሥነ ግጥማዊ ትሩፋቶቹ ከፍተኛ አድናቆት የተቀዳጁ ከመሆናቸዉም በላይ ባለቅኔዉ የደረሰበትን የላቀ ሥነ ጽሁፋዊ ደረጃ የሚያመለክቱ ናቸዉ ።ባቢሌ ቶላ በእንግሊዝኛ የጻፈዉን " ቱ ኪል ኤ ጀኔሬሽን" ፤ " አንድ ትዉልድ ለመግደል - ቀዩ ሽብር በኢትዮጵያ" በሚል ርዕስ በዉብ ቋንቋ ወደ አማርኛ በመመለስ ለተደራሲያን አበርክቷል ። ወደፊት በሚወጡ ዕትሞች ስለጸጋዬ የፖለቲካና የብዕር ሰዉነት ሰፋ ያለ ዳሰሳ ይዘን ስለምንቀርብ ይጠብቁን ።

## 40 አመታት በትግል..

የታገላቸዉ ሁለት መንግሥታት ከነሥርዓታቸዉ ተንኮታኩተዉ ወድቀዋል። ትግሉ ግን ከሌላ አምባገነናዊ ዘረኛ መንግሥት ጋር ቀጥሏል ።ትግሉንና የድርጅቱን እንቅስቃሴ በሚመለከት ኢትዮጵያ ጋዜጣችን ከድርጅቱ ከፍተኛ የአመራር አካል ከአቶ ኢያሱ አለማየሁጋር ቆይታ አድርጋለች። እነሆ ።

ኢትዮጵያ -ኢሕአፓ ለመፈጠሩ ግድ ያለዉ የወቅቱ የኢትዮጵያ ታሪካዊ ማህበረሰባዊና ኢኮኖሚያዊ ዳራ ምን ይመስል ነበር?

አቶ ኢያሱ- ቅድመ የካቲት ኢትዮጵያ ንኁሳዊና ባላባታዊ ስርዓት የሰፈነባት ነበረች ። ጭቆና በሁሉም መስክ አውን የሆነባት ። አብዛኛው አርሶ አደር ገባርና ጪሰኛም ነበር። ምርቱን በሀግ ለባላባቶች፣ ለንጉሳዊ ቤተሰቦች፣ መኳንንቶችና መሳፍኖች ማስረከብ የተገደደ። በሀይማኖትና ብሔረሰብ ደረጃም እኩልነት አልነበረም። የሀገሪቷ ሉዓላዊነትም የተደፈረ ነበር ማለት ይቻላል ። ይህን ሁሉ በመቃወም አያሌ ትግሎች ተካሂደዋል ። የአርሶ አደሮች አመጽ፣ የላባደሩ አድማ፣ የብሄረሰቦች ትግል፣ የተማሪዎች ሰልፍና ተቃውሞ ወዘተ...ሁሉ ታይተዋል ። ይህ ሁሉ የተሰበጣጠረ ትግል ይሰምር ዘንድ ግን የመሪነት ሚና ሊጫወት የሚችል የፖለቲካ ድርጅት መኖሩ የግድ አስፈላጊ በመሆኑ የፖለቲካ ድርጅት ለመመስረት ጥረት ተጀመረ፤ ተደረገ።

ኢትዮጵያ - በኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) ታሪክ ዉስጥ ሚያዝያ 1964 እና ነሐሴ 1967 ተለይተዉ የሚጠቀሱ ጊዜዎች ናቸዉ። ምን ድርጅታዊ ተግባራት ተከናወኑባቸዉ ? የኢሕአፓ የልደት በዓል ብለን የምንዘክረዉስ የትኛዉን ነዉ?

አቶ ኢያሱ- የኢሕአፓ መስራች ጉባኤ የተካሄደው በሚያዝያ 1964 ሲሆን ህልውናው የታወጀው ግን ነሐሴ 26 1967 ነው። ልደቱ በሚያዝያው ነው መባሉ ትክክል ነው ።

ኢትዮጵያ -ኢሕአፓ መስራች ጉባዔዉን ካካሄደ ብኋላ ህልዉናዉን ለማብሰርና ድርጅታዊ መርሐግብሩን ለማወጅ ከሶስት ዓመታት በላይ ወስዶበታል ። ምክንያቱ ምንድነዉ ?( ምክንያቶቹ ምንድናቸዉ?)

አቶ ኢያሱ-በመጀመሪያ በህቡዕ ይሰራ ስለነበር ነው ። አቅሙን ከማጠናከሩ በፊት አለሁ ማለቱን አልፈለገም ።

ኢትዮጵያ - ድርጅቱ ራሱን በይፋ ለማሳወቅ ምን ዘዴ ተጠቀመ? በወቅቱስ ሕዝቡ እንደምን ተቀበለዉ?

አቶ ኢያሱ - በመላ ኢትዮጵያ መርሀ ግብሩን ወይም ፕሮግራሙን በልዩ ልዩ ቋንቋዎች - በእንግሊዝኛ ጭምር -- አሰራጩ ። ሕዝብ በደስታ ነበር የተቀበለው ።

ኢትዮጵያ -ኢሕአፓ ከጅምሩ አንስቶ እስከዛሬ ህቡእ ድርጅት ሆኖ የመቆየቱ ምስጢር ምንድነዉ?

አቶ ኢያሱ በይፋ እንዳይሰራ ስለታገደ ነው ። የአገዛዞች አፈናና ጥቃት ሰለባ ስለሆነ ነው ።

ኢትዮጵያ -" ዴሞክራሲያ" ከምስረታ እስከዛሬ የድርጅቱ ልሳን ነዉ ። ከአሰያየም አንስቶ በልሳንነቱ እስከተጫወተዉ ሚና በዝርዝር ቢገልጹልን?

አቶ ኢያሱ- ከህዝብ ትግል አንጻር ደሞክራሲያ በአንቂነት አስተማሪነት ከፍተኛ ሚና ነበረው፤ ዛሬም አለው ። ዴሞ እንደ ዶሞትፎር የተባለው አለምክንያት አልነበረም፤ አይደለም ። የዴሞን ቦታ ሊወስድ የቻለ ሌላ ልሳን የለም ።

ኢትዮጵያ -ኢሕአፓ 40ኛዉን የልደት በዓሉን ያከብራል ። የነዚህን ዘመናት የድርጅቱን ዐበይት እንቅስቃሴዎች እንደምን ይገመግሟቸዋል?

አቶ ኢያሱ- ይህ ሰፊ ርዕስ ነው ። ከአጼው ዘመን ጀምሮ የተካሄደውን ትግል ይጠቅልላል ። ጸረ ወያኔው የኢሕ አፓ ትግል ደግሞ ከ1967 ጀምሮ ነው ። ለሀገርና ለሕዝብ የተደረገ ትግል ነውና የሚደገፍና የሚመሰገንም ነው ። በተግባር የተሰማራ ስህተት ሊፈጽም ይችላልና ኢሕአፓም ከተመከሮ ማነስ የፈጸማቸው ስህተቶች ነበሩ ። በአብላጫው ግን የኢሕአፓ ትግል ሕዝባዊና የሚያኮራ ነው ።

ኢትዮጵያ -ቀይ ሽብር በኢሕአፓ ሕልዉናና እንቅስቃሴ ላይ ምን ጉዳት አስከተለ?

አቶ ኢያሱ- ያደረሰው ጉዳት በጣም ከፍተኛ ነው ። ይሆን ግን ለመወጣት ትግል ተካሂዶ ያው ድርጅቱ ህልውናውን ጠብቆ ትግል እያካሄደ ነው ።

ኢትዮጵያ-ድርጅቱ በሚከተለው ርዕዮተ ዓለምና በሚተገብራቸዉ መርሐ ግብሮች ረገድ ለዉጥ አድርጓል? መቼና የትኞቹን?

አቶ ኢያሱ- ከሁኔታዎች አንጻር ድርጅቱ ተገቢውንና አስፈላጊ የሆኑትን ለውጦች አድርጓል ። መሬት ለአራሹ በሚለው ላይ ፤ ቡበሄረ ሰቦች መብት ጥያቄ ላይና ወዘተ... ዛሬ ኢሕአፓ ከርዕዮት አንጻር ህብረሰባዊ ዴሞክራሲ ወይም ሶሻል ዴሞክራሲ ነው ። የሰፊውን ሕዝብ መሰረታዊ ፍላጎት ማስቀደም ።

ኢትዮጵያ -ከምሥረታ እስከዛሬ ስንት ጉባዔዎችን አካሄደ? የትና መቼ ፤ በጉባዔዎቹስ ምን የተለየ ክንዉን አስመዘገበ?

አቶ ኢያሱ- እስካሁን አራት ጉባኤና አንድ ልዩ ጉባኤ አካሂዷል። ሁሉም ጉባኤዎች የየራሳቸው ሚዛን ነበራቸው ። ሚዛናቸውም ከፍተኛ ነው

ኢትዮጵያ -ኢሕአፓ በአሁኑ ወቅት በአገር ቤትና በዉጭ አገሮች የሚያደርጋቸዉ እንቅስቃሴዎች ምን ይመስላሉ ?

አቶ ኢያሱ- ኢሕአፓ ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ ትግሉን ቀጥሏል ። ከዚህ ባሻገር ዝርዝሩ የሚታይ እንጂ መነገር ያለበት አይደለም ።

ኢትዮጵያ - በፖለቲካ ድርጅቶች የህብረት ጥያቄ ላይ ኢሕአፓ ያለዉ አቋም ምንድነዉ?

አቶ ኢያሱ -ህብረት የሚሉ ይተባበሩ ። ኢሕአፓ ግን ህብረት በትግሉ መድረክ በሀገር ቤት ይሁን ባይ ነውና በዚያ እንተባበር ሲል ጥሪውን አስተጋብቷል ። እስካሁን ምላሽ አላገኘም ።

ኢትዮጵያ -40ኛዉን የልደት በዓል አስመርኩዘዉ ለኢትዮጵያዉያን የሚያስተላልፉት መልዕክት(ቶች)?

አቶ ኢያሱ-ባለን አቅም ጥረት አድርገን 41ኛውን በሀገራችን ለማክበር እንጣር።

## የዋንጫው አሸናፊ...

በቴክሳስ ዳላስ ከተማ በተደረገው 29ኛው የኢትዮጵያውያን እግር ኳስ ውድድር በሰሜን አሜሪካ አሸናፊ የሆነው የሜሪላንድ ቡድን፣ በጁላይ 29/2012 በአቢሲኒያ ሬስቶራንት የምሳ ግብዣ ተደረገለት።።

በዚህ የምሳ ግብዥ ሥነ-ስርዐት ላይ የሜሪላንድ ቡድን እግር ኳስ ተጫዋቾችን ጨምሮ ሌሎች በርካታ ደጋፊዎች የተገኙ ሲሆን፣ በእለቱ የተደረጉ የሜዳሊያ ሽልማት ስጦታዎች እና የእግር ኳስ ቡድኑን አስመልክቶ የተደረጉ አጫጭር ንግግሮች እንዲሁም በዋንጫው ዙሪያ የማስታዎሻ ፎቶ ግርፍ ለመነሳት ታዳሚው ያሳየው ፍላጎት ለዝግጅቱ

## ዝግጅቱ በእጅጉ የተሳካ

**ነበር...** ተራ አይነት ሳይሆን በአገራችን የታወቁ እስከስታ ተጫዋቾች የሚያደርጉት አይነት ፕሮፌሽናል ብቃት ያለዉ እንቅስቅሴ ነበር፣ ለዚህም ከታዳሚው በኩል ተደጋጋሚ የአድናቆት ጭብጨባ ተቸርታል።

ዝግጅቱ ማራኪና አስድሳች ሆኖ ያመሸ ሲሆን፣ ከመፈጸሙ በፊት የኢወክንድ ወጣቶች በህብረት በዘመሩት «ልጓዝ በድል ጎዳና» መዝሙር ተጠናቋል።

ልዩ የሆነ ድምቀት የሰጡት ትእይንቶችነበሩ።
በዝግጅቱ ላይ የፌደሬሽኑ ፕሬዚዳንት አቶ ጌታቸውን ጨምሮ በርካታ ታዋቂ ግለሰቦች የተገኙ ሲሆን አንጋፋው አርቲስት ማህሙድ አህመድ የእግር ኳስ ቡድኑ የበላይ ጠባቂ ተደርጎ ተመርጧል። አርቲስት ማህሙድ አህመድ፣ ለእግር ኳስ ቡድኑ የበላይ ጠባቂ ተደርጎ መመረጡን በደስታ የተቀበለ ሲሆን፣ ወደፊት በእርሱ የበላይ ጠባቂነት ዘመን ቡድኑ ተጨማሪ ዋንጫዎችን አሸንፎ እንደሚያመጣ ያለውን ተስፋ ለታዳሚው አረጋግጧል።
የኢትዮጵያ የእግር ኳስ ፌደሬሽን በሰሜን አሜሪካ ዘንድሮ ለ29ኛ ጊዜ ባዘጋጀው በዚህ የእግርኳስ ውድድር፣ የሜሪላንድ ቡድን የዲሲ አቻውን አሸንፎ ዋንጫውን ለሶስተኛ ጊዜ ወስዷል።




የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌደሬሽን በሰሜን አሜሪካ፣ በሚቀጥለው አመት ለ30ኛ ጊዜ የሚደረገውን የእግር ኳስ ውድድር በዋሽንግተን ዲሲ እንደሚያደርግ የሚጠበቅ ሲሆን፣ በዚህ ውድድር ላይ የሜሪላንድ ቡድን ጠንካራ ተፎካካሪ ሆኖ ለመገኘት ከወዲሁ ዝግጅቱን እንደሚጀምር በዕለቱ በዝግጅቱ ላይ ከተደረጉ ንግግሮች ለመረዳት ችለናል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ፣ ወያኔ ለረጅም አመታት ስደተኛውን ኢትዮጵያዊ በዚሁ የእግር ኳስ ጨዋታ ዙሪያ ሲያሰባስብ የቆየውን፣ በሰሜን አሜሪካ የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌደሬሽንን በገንዘብ ሀይል ለማፍረስና የራሱን ተለጣፊ ቡድን በመፍጠር እውነተኛውን ፌደሬሽን ለማዳከም ያደረገው ሙከራ፣ በፌደረሽኑ ውስጥ ባሉ ጠንካራ ሰዎች እና በስደተኛው ኢትዮጵያዊ ማህበረሰብ ጠንካራ ትግል ሙሉ በሙሉ ሊከሽፍ ችሏል። ወያኔ በጁላይ 1/2012 በዋሽንግተን ዲሲ ውስጥ ከዳላሱ በተቃራኒ የእግር ኳስ ውድድር ለማድረግ የሞከረ ቢሆንም፣ በስታዲየሙ ውስጥ የተጠበቀውን ያህል ሰው ባለመገኘቱ እና ሰው አልባ ስታዲየም ይዞ በመቅረቱ፣ አዘጋጆቹ ከፍተኛ ሽንፈት ደርሶባቸው በሀፍረት ለመሸማቀቅ በቅተዋል።

በሼክ መሀመድ አላሙዲ የገንዘብ ኢጋፋሪነት ወያኔ ፌደሬሽኑን ለማፍረስ ያደረገው ከንቱ ሙከራ የከሸፈው፣ በስደት ላይ ባለው ኢትዮጵያዊ ማህበረሰብ ከፍተኛ ጥረት መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን፣ ወደፊትም ይኼው ማህበረሰብ እንደ አንድ ሰው በመሆን ፌደሬሽኑን ከማንኛውም የመከፋፈል አደጋ እንደሚጠብቀውና ቀጣይ እድሜ እንዲኖረው ለማስቻልም ማንኛውንም እርዳታ ሊያደርግለት እንደሚገባ የብዙ አገር ወዳድ ዜጎች ሁሉ እምነት ነው።

## መፍትሔው ምንድን ነው?...

5ኛ.ወያኔ፣ በጁላይ 13 እና 21 በአንዋር መስጊድ ያደረሰው የሰብአዊ መብት ጥሰት በገለልተኛ ወገን እንዲጣራ።

6ኛ.የወያኔ የጸጥታ ሀይሎች በወሰዱት የሀይል እርምጃ ሰለባ ለሆኑት ወገኖች የህክምና ድጋፍ እንዲደረግላቸውና ከፍተኛ የአካል ጉዳት ለደረሰባቸው እና ህይወታቸውን ላጡ ወገኖች ደግሞ ካሳ እንዲከፈላቸው።

7ኛ.በሚዲያ የሚደረገው የጥላቻ ፕሮፓጋንዳ እንዲቆም እና የሀይማኖት መሪዎችን፣ ጋዜጠኞችንና በጠቅላላው የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ላይ እየደረሰ ያለው እስር እና እንግልት እንዲቆም ሲሉ ጠይቀዋል።

**ባስኪን ሮቢንስ ዳንኪን ዶናት ደንበኞችን ማስተናገድ የሚችሉ ሰራተኞችን መቅጠር ይፈልጋል፤ የሥራ ሰዓት ከ4 ሰዓት እስከ 5 ጠዋት ማልዶ መግባት የሚችል።**

**አድራሻ**
**2420 New york Ave NE. Washington DC. 20002**
**ስልክ፡-202-326-367**

